በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የቦሌ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት
የ2018 ዓ. ም የመጀመሪያ ወሰነ ትምህርት የ6ኛ ክፍል የአማረኛ ቋንቋ ትምህርት
ሞዴል ፈተና

የጥያቄ ብዛት፡- 40 የተፈቀደው ሰዓት፡- 1 ሰዓት

አጠቃላይ ትዕዛዝ

ይህ ፈተና የአማርኛ ቋንቋ ነው፡፡ በዚህ ፈተና ውስጥ 40 ጥያቄዎች ተካተዋል፤ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሚሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምረጥ ለመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል ፡፡በፈተና ላይ የተሰጡትን ትዕዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል፡፡ መልስ የሚሰጠው ከፈተናው ጋር በተያያዘ መልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው፡፡ በዚህ ወረቀትላይ ትክክለኛ መልስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው፤ ትክክለኛ መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደውን ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጠቆር አለበት፤ የተጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢያስፈልግ በፊት የተጠቆረውን በደንብ ማጥፋት አለባችሁ፡፡

መልስ የሚሰጠው በመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ብቻ ነው፡፡ ለምሳሌ መልሳችሁ ለ ከሆነ ከታች በሚታየው መልክ ማጥቆር አለባችሁ፡፡

| ሀ | ለ | ሐ | መ |
|---|---|---|---|
| ○ | ● | ○ | ○ |

ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተፈቀደው ሰአት 1:00 ሰዓት ነው፡፡ ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን እርሳስ ማስቀመጥና መስራት ማቆም አለብን፡፡ ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ (በፈታኟ) እስከሚነገር ድረስ በቦታችሁ ተቀምጣችሁ መጠበቅ አለባችሁ፡፡መኮረጅ ወይም በፈተና ሰአት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ ወይም ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል፡፡
ፈተናውን መስራት ከመጀመራችሁ በፊት መልስ መስጫ ወረቀት ላይ መሞላት የሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት ፡፡

ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መስራት አይፈቀድም !

መልካም እድል !



LIVEWORKSHEETS

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የቦሌ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የቦሌ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የ2018 ዓ. ም የመጀመሪያ ወሰነ ትምህርት

ሞዴል ፈተና

---

መመሪያ አንድ ከተራ ቁጥር 1 — 5 ያሉትን ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ (ቅንጭብ ጽሑፍ) ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ምንባቡን በሚገባ በማንበብ ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል <u>ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጪ።</u>

… ስነ ጽሁፍ የሰው ልጅ ገጠመኝ ማንፀባረቂያ የሰው ልጅ የህይወት መልኮች መገለጫ ነው። የሰው ገጠመኝ እና የህይወት መልክ ደግሞ ስፍር ቁጥር የለውም ። ህይወት ባለ ብዙ ፈርጅ ባለብዙ ቀለም መሆኑም ግልፅ ነው። ስለዚህ የስነፅሁፍ ክልል እዚህ ድረስ ነው ተብሎ ሊገደብ አይችልም ማለት ነው። ስነ ፅሁፍ ማንኛውም የሰው ልጅ ገጠመኝ የተከሰተንና ሊከሰት የሚችል ነገር እንዲሁም በሰው የምናብ አድማስ ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚታሰብን ነገር ሁሉ ሊያካትት ይችላል ። መጠነ ርዕዩ እጅግ ሰፊ ብቻም ሳይሆን ገደብ አልባ ነው። የሰው ልጅ ተግባራት በምናቡ የሚፈጥረው በአለም ላይ ያሉ ፍጡራን በሰው እና በሰው መካከል የሚፈጠሩ ግንኙነቶች በስነ ፅሁፍ ውስጥ እንዳስፈላጊነታቸው ሊካተቱ ይችላሉ።ስነ ፅሁፍ በነዚህ በተጠቀሱት ግንኙነቶች ውስጥ የሚከሰቱትን ተቃርኖዎችንና ህልውናዊ ትግሎች ይይዛል።

ምንጭ ( ዘሪሁን አስፋው የስነ ፅሁፍ መሰረታውያን)

1. የስነ-ፅሁፍ ክልል እዚህ ድረስ ነው ተብሎ ሊገደብ አይችልም። የተባለው ለምንድን ነው?

   ሀ ህይወት ባለብዙ ፈርጅ ስለሆነች

   ለ. ስነፅሁፍ የፈጠራ ስራ በመሆኑ

   ሐ. ስነ ጽሁፍ የሰው ልጅ ገጠመኝ ማንፀባረቂያ ስለሆነ

   መ. መልስ የለም

2. በፅሁፉ መጀመሪያ ላይ ያለው ስርአተ ነጥብ ምንን ያመለክታል?

   ሀ. ሀሳቡ የሚቀጥል መሆኑን

   ለ. የተቆራረጠ ሀሳብ መያዙን

   ሐ. ተቆርጦ የቀረ ሃሳብ መኖሩን

   መ. ሁሉም

LIVEWORKSHEETS

3. አያሌ ለሚለው ቃል አውዳዊ ፍቺው __________ ነው።

ሀ. ትንሽ ሁ. ብዙ ሐ. መልክ መ. መልስ የለም

4. ገደብ አልባ ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ፍቺው __________ ነው።

ሀ. መጨረሻ የሌለው ለ. ስርአት አልባ

ሐ. መጨረሻ ያለው መ. መልስ የለም

5. እንደ ምንባቡ አገላለፅ ስነፅሁፍ ____________ ነው።

ሀ. የሰው ልጅ ገጠመኝ ማንፀባረቂያ

ለ. የተከሰተን እና ሊከሰት የሚችልን ነገር ማሳያ

ሐ. የህይወት መልክ መግለጫ

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

መመሪያ ሁለት ከተራ ቁጥር 6 - 40 ድረስ የተለያየ ይዘትያላቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል። እያንዳንዱ ጥያቄ በጥሞና በማንበብ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጪ።

6. ከተሰጡት አማራጮች መካከል በፍቺ ልዩ የሆነው ቃል የትኛው ነው?

ሀ. አልቦ ለ. ጥቂት ሐ. ባዶ መ. ምንም

7. "መከራት" በሚለው ቃል የተጨመረው ድህረ ግንድ ቅጥያ የቱ ነው?

ሀ. ት ለ. አት ሐ. ኡ መ. ኡት



LIVEWORKSHEETS

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የቦሌ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት
የ2018 ዓ. ም  የመጀመሪያ ወሰነ ትምህርት የ6ኛ ክፍል የአማረኛ ቋንቋ ትምህርት
ሞጁል ፈተና

8. በለጠና ዮናስ ትላንትና ከአዳማ ይመጣሉ። ይህ ዓ/ነገር ሰዋሰዋዊ ስህተቱ ተስተካክሎ ሲፃፍ ትክክለኛው የቱ ነው?

ሀ. በለጠ ይመጣል ከአዳማ ትናንትና ።

ለ. በለጠ እና ዮናስ ትናንትና ከአዳማ መጡ።

ሐ. በለጠና ዮናስ ትናንትና የመጡ ከአዳማ ።

መ. በለጠና ዮናስ ከአዳማ ይመጣሉ ትናንትና።

9. ሔርሜላ <u>ነብር</u> ናት። የተሰመረበት ቃል ፍካሬያዊ ፍቺ ሊሆን የሚችለው ቃል የቱ ነው?

ሀ. ስጋ በል የዱር እንስሳት    ለ. የዋህ    ሐ. ፈጣን    መ. ተንኮለኛ

10. ከሚከተሉት መካከል <u>የአንቀፅ</u> ተዋቃሪ አካላት የሆኑት የትኞቹ ናቸው?

ሀ/ ርዕስ እና መዘርዝር    ለ/ ሀይለቃል እና መደምደሚያ

ሐ/ ሀተታና መዘርዝር    መ/ ሀይለቃል እና መዘርዝር

11. አንድ ነገር መቼ እንደሚከሰትና እንደተከሰተ የሚነግረን የቃል ክፍል______ ነው?

ሀ. ግስ    ለ. የሁኔታ ተውሳከ ግስ    ሐ. ስም    መ. የጊዜ ተውሳከ ግስ



12. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የገጸ ባህሪያትን ንግግር ለማስቀመጥ የሚያገለግለን የስርአተ ነጥብ አይነት የቱ ነው ?

ሀ ትዕምርተ ጥቅስ    ለ ነጠላ ሰረዝ    ሐ/ ቅንፍ    መ/ ድርብ ሰረዝ

13. ህፃኑ ስለራበው አምርሮ አለቀሰ። በዚህ ዐ.ነገር ውስጥ የሁኔታ ተውሳከ ግስ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. አምርሮ    ለ. ስለራበው    ሐ. ህፃኑ    መ. አለቀሰ

14. ከሚከተሉት ቅርፆች መካከል ሀይለ ቃሉ መጀመሪያ ሲመጣ የትኛውን ቅርፅ እንጠቀማለን?

ሀ/     ለ/     ሐ     መ 



LIVEWORKSHEETS

15. የውስጥን ስሜት አውጥተን በመናገር መፍትሔ ሲገኝ እንደሚቻል የሚያመላክት ምሳሌያዊ አነጋገር የትኛው ነው?

ሀ. ያልጠረጠረ ተመነጠረ — ለ. በሽታውን የደበቀ መድኃኒት የለውም

ሐ. አልሞት ባይ ተጋዳይ — መ. የሚወዱትን አቅፍ የጠሉትን ንቅፍ

16. ስለአንቀፅ ትክክል የሆነው አገላለፅ የቱ ነው?

ሀ. በውስጡ መዘርዝር ዐ/ነገሮችን ይይዛል።

ለ. የአንቀፁን ዋና ሀሳብ የሚገልጽ ዐ/ነገር ይይዛል።

ሐ. አንቀፅ አንድ ዋና ሀሳብ ብቻ ይኖረዋል።

መ. ሁሉም መልሶች ናቸው።

17. ከሚከተሉት ቃላት ቅድመ ግንድ ቅጥያ ያለው ቃል የቱ ነው?

ሀ. መከራት — ለ. ገንዘባችን — ሐ. ተማሪዎች — መ. ስለወደቀች

18. ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ለተጸውዖ ስም ምሳሌ ሊሆን የሚችለው ______ነው።

ሀ. ተራራ — ለ. ወንድ — ሐ. መምህር — መ ኬንያ

19. ቢንያም የአቶ ተመስገን የበኩር ልጅ ነው። የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ የሚገልጸው የትኛው ነው?

ሀ. የስስት — ለ. የመካከል — ሐ. የመጀመሪያ — መ.የመጨረሻ

20. በሁለት ተጣማሪ ቃላት መሃል እየገባ ፣ ጥምር ቃልን ለመመስረት የሚያገለግል የስርዓት ነጥብ ምልክት የትኛው ነው?

ሀ.ነጠላ ሰረዝ — ለ. ሰረዝ — ሐ. ድርብ ሰረዝ — መ. አራት ነጥብ



LIVEWORKSHEETS

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የቦሌ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የቦሌ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የ2018 ዓ. ም የመጀመሪያ ወሰነ ትምህርት የ6ኛ ክፍል የአማረኛ ቋንቋ ትምህርት ሞዴል ፈተና

21. ቀጥሎ የቀረበው ቃላዊ ግጥም በምን ጊዜ የሚገጠም ነው ?

ሆ! ይላል ገበሬ x 2

ድብ እያፈረሰ በሽልማ በሬ!

በርቄ በርቄ አንተን የቻለ ሰው!

ቶሎ ቶሎ ብለህ እንጆቱን አርሰው ::

ሀ .እርሻ  ለ . ለቅሶ  ሐ . ሰርግ  ለ . ሁሉም

22. ከሚከተሉት ውስጥ የግስ ተግባር የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. በዓረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤት በመሆን ያገለግላል

ለ. የሃሳብ መቋጫ በመሆን ያገለግላል

ሐ. የስም ገላጭ በመሆን ያገለግላል

መ. ተሳቢ በመሆን ያገለግላል

23. ከስነ ፅሁፍ አላባውያን ወስጥ ታሪክ የተፈፀመበት ጊዜና ቦታ ምን ይባላል ?

ሀ. ግጭት  ለ. ትልም  ሐ. መቼት  መ. ጭብጥ

24. የሰሞኑ ብርድ ሃይለኛ በመሆኑ ፣ ቆፈኑ ሊያንቀሳቅሰኝ አልቻለም :: የተሰመረበት ቃል ተቃራኒ ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?

ሀ. ቅዝቃዜ  ለ. ሙቀት  ሐ. ብርሃን  መ. ብርድ

25. ስለገንዘቦቻቸው ለሚለው ቃል የምዕላድ አከፋፈሉ ትክክል የሆነው አማራጭ የቱ ነው?

ሀ. ስለ - ገንዘብ- ኦች - ኣቸው  ለ. ሰ- ለ - ገንዘብ - ቻ- አቸ- ው

ሐ. ሰለ - ገንዘብ - ኦች- ቸው  መ. ስለገን - ዘብ - አቸው



LIVEWORKSHEETS

26. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል "የአለባበሶቻችን" የሚለው ቃል ተነጣጥሎ የቀረበው በየትኛው አማራጭ ነው?

ሀ. የአለባበሶች-ቻችን　　ለ. የአለባበስ-ኦች-አችን

ሐ. የ-አለባበስ-አች-አችን　　መ. የ-አለባበስ-አቻችን

27. የወል ስምን በተመለከተ ትክክለኛ ሀሳብ የያዘው የቱ ነው?

ሀ/ የጋራ መጠሪያ ሲሆን ለምሳሌ ያህል አየለ፣ መዓዛና ተራራ ተጠቃሾች ናቸው

ለ/ የግል መጠሪያ ሲሆን ለምሳሌ ያህል ወንዝ፣ ቤት፣ ሴት ተጠቃሾች ናቸው

ሐ/ የጋራ መጠሪያ ሲሆን ለምሳሌ ያህል ቤት፣ ተማሪ፣ ት/ቤት ተጠቃሾች ናቸው

መ/ መልስ አልተሰጠም

28. "በላይ ዘለቀ በ19 02 በጎጃም ተወለዱ። አስራአራት አመት እስኪሞላቸው ድረስ በግብርና ስራ ይተዳደሩ ነበር።" ይህ ጽሁፍ ከየትኛው የድርሰት አይነት ይመደባል?

ሀ. ከገላጭ ድርሰት　　ሐ. ከአከራካሪ ድርሰት

ሊ. ከተራኪ ድርሰት　　መ. ስዕላዊ ድርሰት

29. ሰዎች ከዚህ ዓለም በሞት በሚሰናበቱበት ጊዜ በወዳጅ ዘመድ የሚዜም ቃላዊ ግጥም _____ ይባላል ።

ሀ. የእንጉርጉሮ　　ሉ. የሙሾ　　ሐ.የልመና　　መ.የልጅ ማባበያ

30. ከሚከተሉት ስሞች መካከል በብዙ ቁጥር ሊገለፅ የሚችለው የቱ ነው ?

ሀ. ጉብዝና　　ሉ. ቃል　　ሐ. ዱቄት　　መ. ፍቅር

31. "ሜላት ለእናትዋ ጋቢ ገዛች። " በዚህ ዓ/ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል _______ ነው ።

ሀ. ርቱዕ ተሳቢ.　　ለ. ኢ-ርቱዕ ተሳቢ.　　ሐ. ሳቢ ግስ　　መ. ግስ



LIVEWORKSHEETS

32. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ ተመሳሳይ ሀሳብ ያላቸውን ዓ/ነገሮችን ለማያያዝ የሚያገለግለው የቱ ነው ?

ሀ. ይሁን እንጂ  ለ. ነገር ግን  ሐ. ስለዚህ  መ. ይሁንና

33. እረፍት ላይ ስላሆንን ወደመዝናኛ ቦታ ሄድን ። በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤቱ ማን ነው?

ሀ. እኛ  ለ. እናንተ  ሐ. እነሱ  መ. አንቺ

34. ከሚከተሉት ቃላት መካከል ባለ ሶስት ምዕላድ  ቃል የቱ ነው ?

ሀ. እንደሄደች  ለ. በሬዎች  ሐ. ሰነፍ  መ. አየች

35. "የጠቡ መንስኤ ምንድን ነው?" በዚህ ዐ.ነገር ውስጥ መንስኤ የሚለው ቃል ዓውዳዊ ፍቺ ምንድን ነው?

ሀ.  መነሻ  ለ. ምክንያት  ሐ. አሸናፊ  መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

36. በዐ/ነገር ውስጥ ስምን ተክተው በመግባት የስምን ሙያ የሚጫወት የቃል ክፍል የቱ ነው ?

ሀ. ስም  ለ. ግስ  ሐ. ተውላጠ ስም  መ. ቅፅል

37. "ጎበዙ ተማሪ መፅሀፍ ተሸለመ ።"በዚህ ዓ/ነገር ውስጥ መፅሀፍ  የሚለው ቃል ሰዋሰዋዊ ተግባር ምንድን ነው ?

ሀ. ባለቤት  ለ. ግስ  ሐ. ተሳቢ  መ. መስተዋድድ

38. "ልጆቹ ከትምህርት ቤት መተዋል። "በዚህ ዓ/ነገር የጊዜ ግሱ የተገለፀው ________ ነው ።

ሀ. በየአሁን ጊዜ  ለ. በሀላፊ ጊዜ  ሐ. በትንቢት ጊዜ  መ በወደፊት ጊዜ



LIVEWORKSHEETS

39. ከሚከተሉት መካከል በሁኔታ ተውሳከ ግስ የተገለፀው ዓ/ነገር የቱ ነው ?

ሀ. አለም ነገ ትመጣለች ።

ለ. መምህሩ ስለመጣ ዝም በሉ ።

ሐ. ተማሪው ስለረፈደበት እየሮጠ ሄደ።

መ. እናቴ እቤት የለችም ።

40. ፣ ከሚከተሉት ቃላት ውስጠ ግንድ ቅጥያ ያለው ቃል የቱ ነው?

ሀ. አጫጭር    ለ. መምህራን    ሐ. መንገድ    መ . ስለሄደ



LIVEWORKSHEETS